# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

## JAMHUURIYADA DIMUQURAADIGA FEDERAALKA ITOOBIYA

# JARAAIDKA FAAFINTA RASMIGA EE FEDERAALKA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፬ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Sanadka 23aad Tirsi. 7
ADDIS ABABA 23kii Disember, 2016


**አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፭/፳፻፲፮ ዓ.ም**


የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ…………ገጽ ፱ሺ፬፻፴፮


**Bayaan Tirsi. 985/2016**


Bayaanka Ururrada Iskaashatooyinka……Page 9436

## አ ዋጅ ቁጥር አ ዋጅ ቁጥር,-.//12፱ ዓ ም.

## ስ ለ ኅብረ ት ሥራ ኅብረ ት ሥራ ማህበ ራት ማህበ ራት የወጣ አዋጅ

ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኅብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ ዕውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶችን በማሟላት እርስ በርስ መደጋገፍንና ቁጠባን የሚፈጥሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማቋቋም እና መምራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠር እና በከተማ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በአባላት ምርት ላይ ዕሴት በመጨመር፣ የግብይት እና የፋይናንስ ትስስር በመፍጠር፣ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትን በማሳጠር፣ በሃገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆን ለዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር በሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት በአንድ ወጥ ሃገራዊ፤

የኅብረት ሥራ ማህበር አዋጅ በመመራት በሕገ መንግስታችን አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሏቸውን መሠረታዊ መርሆዎችና ልዩ ባህሪ እንደጠበቁ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶ ፭(፮) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**BAYAAN TIRSI. 985/2016**

## BAYAANKA URURRADA ISKAASHA-TOOYINKA

MAADAAMA, ay lagama maarmaan noqotay in dadka dan-wadaagta ah loo aasaaso nidaam iyo ururro iskaashato iyaga oo si iskood ah iskugu darsanaya lacagahooda, aqoontooda, maalkooda (khayraadkooda) iyo cududdooda si ay u daboolaan baahiyahooda ay ka siman yihiin ee dhaqaale, bulsho iyo dhaqan iyo [sidoo kale] yidid iilooyinkooda kale taas oo u saamaxi doonta in ay is garabsadaan oo ay abuurtaan kayd hantiyeed.

MAADAAMA, ururrada iskaashatooyinka looga baahanyahay in ay qayb ka noqdaan dhaqaalaha iyo horumarinta bulsheed ee dalka, in ay noqdaan kuwo leh awood ay kaga tartami karaan suuqyada heer dal iyo heer caalami, in ay abuuraan fursado shaqo iyaga oo kaalin ka geysanaya waxsoosaarka iyo kor u qaadista heerka waxsoosaarka miyi iyo magaalaba, dheef-kordhinta/qiimo kordhinta waxasoosaarka xubnaha, abuurista isku xidhka maaliyayeed iyo suuqa, yaraynta/gaabinta silsiladdaha xidhiidhka suuqyada ee aan loo baahnayn, hab wax wartar u leh joogtaynta hal dhaqaale bulsheed si waafaqsan dastuurkeena, iyada oo la raacayo bayaan midaynaya [qaab-dhismeedka] urrada iskaashatooyinka.

MAADAAMA, ay lagama maarmaan tahay in ururrada iskaashatooyinku door wada jir ah ka ciyaaraan nidaamka dhaqaalaha suuqa xorta ah iyaga oo raacaya mabaadii'dooda iyo sifooyinkooda gaarka ah.

MAADAAMA, ay lagama maarmaan tahay in la aasaaso lana xoojiyo ururro iskaashato oo

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የ ኅ "ብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፱ ፻ ፹ ፭/ ፪ሺ፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እና በተናጠል ሊፈቱ ያልቻሏቸውን ችግሮች በጋራ ለማቃለል ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት የሚያቋቁሙት፣ በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሠረት የሚመሩትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚቆጣጠሩት ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር ነ ው፤

፪/ "መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት የጋራ ፍላጎት እና ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ለማምረት፣ አገልግሎት ለመስጠት ወይም ሁለቱንም ለማከናወን የሚቋቋም የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፫/ "የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን" ማለት ተመሣሣይ ዓላማ ባላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ የሆነ የማምረት፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ለመፈፀም ሚቋቋም ሁለተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

ay hagistooda iyo maamulkoodaba leeyihiin xubno wada jira sidoo kalena la sugo xuquuqahooda, mulkiilayaashooda iyo faa'iidooyinka ay ka helayaan.

MAADAAMA, ay lagama maarmaan tahay in dalka la wada gaadhsiiyo qawaaniinta aasaaska ururrada iskaashatooyinka iyada oo laga guurayo qawaaniinta aasaaska ururrada iskaashatooyinka ee hadda jira, si loo hanto yoolka ururrada iskaashatooyinka.

HADDABA, SIDAA DARTEED, iyada oo la raacayo qodobka 55 (6) ee Dastuurka Jamhuuriyada Federal Dimoqraadiga Ethiopia, waxa halkan lagu bayaaminaya sidan soo socota:

**QAYBTA KOOWAAD**

**GUUD AHAAN**

1. **Ciwaan Gaaban**

   Bayaankan waxa loo tix-raacayaa sidan "Bayaanka Ururrada Iskashatooyinka Tirsi. 985/2016"

2. **Qeexid**

   Bayaankan dhexdiisa, haddii aanu micnaha nuxurku u baahan si ka duwan, weedhahan soo socda waxa loola jeedaa:

1/ "**Urur iskaashato**" macnihiisu waa urur madax banaan oo leh jiritaan sharci kaas oo ay si dimoqraadiya u maamulaan shaqsiyaad u shuraakoobay si iskood ah si ay iskaga kaashadaan baahiyahooda dhaqan-dhaqaale, iyo bulsheed ee aanay iskaga kaafiyi karayn si keli keli

፬/ “የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን” ማለትተመሣሣይ ዓላማ ባላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በላይ የሆነ የማምረት፣አገልግሎት የመስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ለመፈፀም የሚቋቋም ሦስተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፭/ “የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችን የሚወክል ሊግ ነው፤

፮/ “ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበር” ማለት ለአባላቱየማምረት እና አገ ልግሎት የ መስጠት ተግባራትን ለማከናወን የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፯/ “የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር” ማለት የቁጠባ፣ የብድር እና የብድር የሕይወት መድን አገልግሎቶችን ለአባላቱ ለመስጠት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፰/ “የብድር የሕይወት መድን” ማለት ከኅብረት ሥራ ማህበር ብድር የወሰደ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ብድሩን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ሳይጨርስ በሞት ቢለይ ቀሪውን ብድር ለመክፈል የሚሰጥ የመድን ዋስትና ነው፤

፱/ “የኅብረት ሥራ ማኅበር የሥራ ክልል” ማለት በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነና አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ የሥራ ክልል ነው፤

ah iyaga oo ku shaqaynaya mabaadii’da iskaashatooyinka.

2/ “**Ururka iskaashatada aasaasiga ah”** waxa loolaa jeedaa urur iskaashato oo ay aasaaseen shaqsiyaad leh dano iyo hadaf isku mid ah kuwaas oo ka kooban tirada xubnaha ugu yar ee lagu cayimay bayaankan dhexdiisa in ay waxsoosaar samayn karaan, in ay adeegyo bixin karaan ama in ay labada hawloodba ka shaqayn karaan.

3/ “**Dalladda Ururrada iskaashatooyinka”** waxa loolaa jeedaa urur iskaashato oo heerka labaad ah oo ay aasaaseen shaqsiyaad leh dano iyo hadaf isku mid ah kuwaas oo ka kooban tirada xubnaha ugu yar ee loogu cayimay bayaankan dhexdiisa in ay waxsoosaar samayn karaan, in ay adeegyo bixin karaan ama in ay labada hawloodba ka shaqayn karaan wixii ka baxsan awoodda heerka ururka iskaashatooyinka aasaasiga ah.

4/ “**Midowga ururrada iskaashatooyinka”** waxa loolaa jeedaa urur iskaashato oo heerka sadexaad ah kaas oo ay aasaaseen dalladaha ururrada iskaashatooyin ka kuwaas oo leh dano iyo hadaf isku mid ah islamarkaana ka kooban tirada xubnaha ugu yar ee loogu cayimay bayaankan dhexdiisa in ay waxsoosaar samayn karaan, in adeegyo bixin karaan ama in ay labada hawloodba ka shaqayn kuwaas oo ka baxsan heerka awoodeed ee ururrada dallada iskaashatooyinka

5/ “**Naadiga ururrada iskaashatooyinka**” waxa loola jeedaa naadi ay ku bahoobeen ururrada iskaashatooyinka aasaasiga ah dalladaha ururrada iskaashatooyinka iyo midowga ururrada iskaashato kuwaas oo ka hawlgala gudaha dalka Itoobiya.

፲/ “አባል” ማለት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንደኅብረት ሥራ ማህበሩ አይነት የተደነገጉትን የአባልነት መመዘኛዎችን በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለሰብ ወይም መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ነው፤

፲፩/ “ጠቅላላ ጉባኤ” ማለት የአንድ መሠረታዊየ ኅብረት ሥራ ማኅበር ግለሰብ አባላት ወይም ተወካዮቻቸው ወይም ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው፤

፲፪/ “ተወካይ” ማለት አወካከሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሆኖ በመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በግለሰብ አባላት ተወክሎ በጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የሚሰጥ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒ ዬን ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተክቶ በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በመገኘት ድምፅ የሚሰጥ ግለሰብ ነ ው፤

፲፫/ “መተዳደሪያ ደንብ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ፪ የተመለከቱትን ዝርዝሮች አሟልቶ የያዘ፣ አግባብ ባለው አካል የተመዘገበ እና በየጊዜው የሚሻሻለውንም ጨምሮ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የፀደቀ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚተዳደርበት ሕግ ነው፤

፲፬ “ልዩ ውሳኔ” ማለት በአባላቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው በኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሁለት ሦስተኛው ድምጽ መጽደቅ ያለበት ውሣኔ ነው፤

6/ “**Ururka iskaashatooyinka danaha badan**” waxa loola jeedaa urur iskaashato oo loo aasaasay in ay samayso waxsoosaar iyo adeeg bixin ay siinayso isla xubnaheeda.

7/ **“Ururka iskaashatada kaydsiga iyo deymaha”** waxa loola jeedaa urur iskaashato oo loo aasaasay in ay xubnaheeda siiso adeegyada kaydsiga lacagta, deymaha caadiga ah iyo deymaha caymiska nolosha

8/ “**Deymaha caymiska nolosha**” waxa loola jeedaa caymiska uu urur iskaashato siiyo isla xubnihiisa si uu u gudo deyn uu qaatay xubin geeriyooday isaga oo aan deyntii si buuxda iskaga bixin.

9/ “**Aagga shaqqada ee ururka iskaashatada”** waxa loola jeedaa nooca shaqo ama hawlaha khaaska ah ee uu ka shaqeeyo ururka iskaashatadu sida uu dhigayo xeer hoosaadka ururku islamarkaana uga sharciyaysan dawlada.

10/ “**Xubin**” waxa loola jeedaa shaqsi, ama urur iskaashato aasaasi ah ama dallado urur iskaashato ama midowga urur iskaashato kaas oo u diwaangashan islamarkaana aqbalsan xubinimo isaga oo buuxinaya shuruudaha ugu yar ee laga rabo xubinimada ee uu dhigayo xeer-hoosaadku islamarkaana dhaqangelinaya habdhaqanka ururka.

11/ “**Shirweynaha Guud”** waxa loola jeedaa kulan ay isugu yimaaddaan shaqsiyaadka xubnaha ah ama wakiilada/mataleyaasha markuu yahay ururka iskaashatada aasaasiga ah, ama mataleyaasha ururrada iskashatooyinka aasaasiga ah, dalladdaha ururrada iskaashato ama midowga urrada iskaashato markuu ka sarreeyo [heerka] ururka iskaashatada aasaasiga ah.

፲፭/ "የሥራ አመራር ኮሚቴ" ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የአንድን የኅብረት ሥራ ማህበር ሥራዎችን እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮/ "ሥራ አስኪያጅ" ማለት ለኅብረት ሥራ ማህበርሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪ የሆነና በተሰጠው ኃላፊነትና ሥልጣን ገደብ መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን የሚያንቀሳቅስ የሥራ ኃላፊ ነው፤

፲፯/ "ሠራተኛ" ማለት ከአሰሪው የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር በገባው ውል መሠረት የዕለት ተዕለት ሥራዎችን እንዲያካሄድ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፤

፲፰/ "የመጠባበቂያ ሒሳብ" ማለት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከዓመታዊ ትርፉ በሕጉ መሰረት ለመጠባበቂያነት የሚያስቀምጠውና ለአባላት በትርፍ ድርሻነት የማይከፋፈለው ሂሳብ ነው፤

፲፱/ "ካፒታል" ማለት የኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ሀብት ላይ ዕዳው ተቀንሶ የሚቀረው የሀብት መጠን ሲሆን የአባላትን የዕጣ ሽያጭ፣ የመጠባበቂያ ሂሳብ፣ ስጦታ፣ ውርስ እና በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰኑ ፈንዶች እና ኢንቨስትመንቶችን የያዘ ነው፤

፳/ "አግባብ ያለዉ ባለስልጣን" ማለት የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ወይም በክልል የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅን ለማስፈጸም፣ ዘርፉን ለመምራት እና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፤

፳፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

12/ "**Wakiil**" sida ku qeexan xeer-hoosaadka ururka iskaashatada ee khuseeya metalaada, waxa loola jeedaa shaqsi ka mida ururka iskaashatada aasaasiga ah kaas oo ku matalay xubnaha in uu ka codeeyo shiweyanaha golaha guud, ama dalladdaha ururrada iskaashato iyo midowga urarrada iskaashato kaas oo ay ku doorteen shirweynaha guud ee ururka iskaashatada si uu u matalo ama ugu codeeyo shirweynayaasha golaha guud ee ururka iskaashatada.

13/ "**Xeer-hoosaad"** waxa loola jeedaa xeer ama sharci loogu talogalay in lagu maamulo ururka iskaashatada iyo wax-ka-bedelkiisa kaas oo lagu ansixiyey codka sadex meelood labo meelood oo ka mida xubnaha shirweynaha guud islamarkaana ka diwaangashan cidda ku shaqada leh isla markaana waafaqaya faahfaahinta ku cad qodobka 12aad ee bayaankan.

14/ "**Qaraar aan caadi ahayn**" waxa loola jeedaa qaraar lagu ansixiyay aqlabiyada sadex meelood labo meelood oo ka mida xubnaha ururka iskaashatada kaas oo ay dabbaqayaan dhamaan xubnaha ururka.

15/ "**Gudiga maamulka**" waxa loola jeedaa waax ama guddi ay doorteen islamarkaana awood u siiyeen shirweynaha guud in ay qaadaan masuuliyada maamulka shaqooyinka ururka.

16/ "**Maareeye"** waxa loola jeedaa sargaal u xilsaaran maamulka gudiga maaraynta kaas oo qaabilsan fulinta hawlaha maalinlaha ah ee ururka iskaashatada kuwaas oo aan ka baxsanayn xadka ay leedahay awoodda iyo masuuliyada uu xambaarsan yahay.

፳፪/ "የኅብረት ስራ ማህበራት ፈንድ" ማለት ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለተለያዩ የጋራ ጥቅሞች ለትምህርት ወይም ለስልጠና ወይም ለኦዲት አገልግሎት ወይም ለማበረታቻ ወይም ለጥናት እና ምርምር ወይም ለህግ አገልግሎት ወይም ለፕሮሞሽንና ኮሙኒኬሽን እና ለማህበራዊ አገልግሎት የሚያውላቸውን ከኅብረት ስራ ማህበራት ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ በጠቅላላ ጉባዔ ሲወስን የሚገኝገቢ እንዲሁም የኅብረት ስራ ማህበራት ከስጦታ ወይም ከውርስ ወይም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመሥራት ከዕርዳታ እና ከተለያዩ ገቢ ማስገ ኛዎች የተገኙ ገቢዎችን እና የኅብረት ስራ ማህበራት ህልውናቸውን በሚያጡበት ጊዜ የማይከፋ ፈሉት የጋራ ገንዘብና ንብረት የሚሰባሰብበት ፈንድ ነው፤

፳፫/ "የዕጣ ክፍያ" ማለት በኅብረት ስራ ማህበሩ የታወጀ ዋጋ ያለው እና ለአባልነት እንደ መጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተሸጠ ወይም የሚሸጥ ነው፤

፳፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤ ፳ ፭/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፬. የኅብረት ሥራ ማህበር ዓላማዎች

በዚህ አዋጅ መሠረት የ ሚቋቋም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

17/ "**Shaqaale**" waxa loola jeedaa shaqsi fuliya shaqooyinka maalinlaha ah ee uu u igmaday ururka iskaashatadu si waafaqsan heshiiska la kala saxeexday xiligga shaqaalaysiinta.

18/ "**Sanduuqa Kaydka"** waxa loola jeedaa qayb ka mida macaashka dheeraadka ah ee sanadkii uu helo ururku kaas oo aan loo qaybinin xubnaha macaash-wadaagta ah balse uu maalgelin ahaan u dhiteeyo ururka iskaashatadu si waafaqsan xeer-hoosaadka.

19/ **Raasamaal** waxa loola jeedaa hantida soo hadha marka laga jaro qaamaha iyo ergisooyinka ururka iskaashatada waxana ka mida saamiga xubnaha, sanduuqa Kaydka maalgelinta, deeqaha, dhaxalka, maalgashiyada lacagaha maalgelinta ah sida uu u dhigayo xeer-hoosaadka ururku.

20/ "**Hay'adda sharci ee ku shaqqada leh**" waxa loola jeedaa wakaaladda iskaashatooyinka federaalka ama waax kale oo ka dhisan heer deegaan taas oo qaabilsan hirgelinta bayaankan iyo maamulka waaxda ururrada iskaashatooyinka.

21/ "**Deegaan"** waxa loola jeedaa maamul kasta oo waafaqsan qeexitaanka ku cad qodobka 47 (1) ee Dastuurka Dawlada Dimoqraadiga Federaalka Itoobiya iyo maamul-magaalooyinka sida Ismaamulka Addis Ababa iyo Ismaamulka Diridhaba.

22/ "**Sanduuqa maalgelinta Ururrada iskaa-shatooyinka**" waxa loola jeedaa nooc maal gelineed/sanduuq lacageed oo loo aasaasay in ururrada iskaashatooyinka lagaga caawiyo dhinaca waxbarashada, tababarrada, adeeg-ga hantidhawrka, kabka, hawlaha daraa-saadka iyo horumarinta, adeegyada sharciga, kobcinta iyo isgaadhsiinta; iyo

፩/ አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መወጣት፣መቋቋም እና መፍታት፤

፪/ አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ማግኘት፤

፫/ በአባላት ዘንድ በራስ መተማመንን ማጎልበት፤

፬/ ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን በመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብአት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ እና ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማስቻል፤

፭/ የቴክኒክ ዕውቀትን እና የሥራ ፈጠራን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤

፮/ በአባላት መካከል የቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

፯/ ለአባላት የብድር አገልግሎትን በመስጠት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤

፰/ ለአባላት የብድር የሕይወት መድን ዋስትና መስጠት፤

፱/ አባላቱ በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሣራ በጋራ በማካፈል የእያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤

፲/ አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅማቸውንና ባህላቸውን ማጎልበት፡፡

adeegyada arrimaha bulshada iyada oo qayb laga jarayo dakhliga saafiga ah ee u soo xarooda iskaashatooyinka marka uu go'aamiyo shirweynaha guud ee kadib marka hantidhawr la sameeyo iyo sidoo kale dakhliyada ka soo xarooda hadyadaha, dhaxalka, hindiseyaal kala duwan oo mashaariiceed, kaalmooyinka, iyo lacagaha ka soo xarooda hawlaha kale ee dakhli-dhalinta, iyo dakhliga ka soo xarooda lacagta aan qaybsamin iyo hantida saafiga ah ee ka soo hadha marka iskaashatooyinku lacageeyaan/ xaraashaan hantidooda.

22/ **"Bixinta Saamiyada"** waxa loola jeedaa saamiga la yaboohay ee leh qiimaha asalka ah (qiimihii koowaad ee saamigu lahaa markii ururku isku darsanayay) ee shardiga u ah in xubinku bixiyo marka koowaad si uu u helo xubinimada ururka taas oo lagu bixiyo lacag caddaan ah ama hanti ahaan.

23/ "**Shaqsi**" waxa loola jeedaa qof dabiici ah ama jiritaan sharci leh.

24/ Ereyada Bayaankan dhexdiisa lagu sifeeyey labku waxa ay sidoo kale dhaqangal ku yihiin dhedigga.

**3. Xadka Fulineed ee bayaankan**

Bayaankani waxa uu dhaqangal ku yahay dhamaan ururrada iskaashato ee ka aasaasan dalka gudihiisa.

**4. Ujeedada Ururrada Iskaasho**

Urur kasta oo iskaashato oo la dhisay iyada oo la raacayo bayaankan waxa uu yeelan karaa mid ama in ka badan oo ka mida ujeedooyinkan soo socda:

1/ in ay si wada jir ah uga gudbaan, iskaga kaashadaan xallinta caqabadaha dhaqaale

## ፰. የኅብረት ሥራ ማህበራት

## መሠረታዊ መርሆዎች

፩/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅበራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነትግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፣ በማኅበራዊ አቋም፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃሉ፡ ፡እንዲሁም አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ያለው ይሆናል፡፡

፫/ ከትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቀንሶ ከተቀመጠ በኋላ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በገዙት ዕጣ መጠን እና ባደረጉት ተሣትፎ መሠረት ቀሪው ትርፍ ይከፋፈላል፡፡

፬/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር መንግሥትንም ጨምሮ ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ በመበደር ካፒታላቸውን ማሳደግ የሚችሉት የአባላትን ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር በሚያረጋ ግጥ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳደር መብት በሚጠብቅ እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

iyo bulsho ee aanay xubnuhu si keli keli ah ku xallin karin.

2/ Si ay natiijo dhaqaale oo wax ku ool u gaadhaan iyaga oo xubnuhu isku biirinaya cudud, maal iyo aqoon.

3/ si ay xubnuhu u gaadhaan isku filnaasho.

4/ si ay iskaga kaashadaan yarayntа kharashka kaga baxa waxsoosaarka iyo adeeg-bixinta iyo in ay xubnuhu agabka waxsoosaarka iyo adeegyada kale ku helaan qiimo hooseeya islamarkaana suuq fiican ugu helaan badeecaddooda iyo adeegyadooda.

5/ Si loo horumariyo xaaladda dhaqaale ee markaa taagan iyada oo aqoonta iyo farsamada casriga ah loogu bedelo hab ficil ah islamarkaana kor loogu qaado hal-abuurka.

6/ Si kor loogu qaado dhaqanka kaydsiga maalka ee xubnaha.

7/ Si xubnaha loo siiyo deymo islamarkaana kor loogu qaado maalgashiga.

8/ Si xubnaha loo siiyo deymaha caymiska nolosha.

9/ Si loo helo khasaare-sooran ama ay xubnuhu iskaga kaashadaan yarayntа khasaaraha iyo dhaawacyada dhaqaale ee soo gaadhi kara balse aanay ka gaashaaman karin hadii ay keli keli u shaqeeyaan.

10/ Si kor loogu qaado tahalka ama awoodda dhaqaale, dhaqan iyo bulsho ee xubnaha iyadoo laga kobcinayo waxbarashada iyo tababarrada.

፭/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ፭/የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና

፮/ በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅሮች ጋር በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን በማጠናከር አባሎቻቸውን በሚገባ ያገለግላሉ፡፡

፯/ የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎቹ ባፀደቋቸው ፖሊሲች አማካኝነት በአካባቢያቸው ላለው ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ፡፡

፮. የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ራስን በራስ መርዳት

ለ) የግል ሃላፊነትን መወጣት፤

ሐ) የዴሞክራሲ ባህልን ማስፋፋት፤

መ) እኩልነት፤

ሠ) ፍትሃዊነት፤

ረ) ወንድማማችነት፡፡

፪ / የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ ምግባር እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

## 5. Mabaaii'da Hagaya Ururrada Iskaashatada

1/ Ururrada iskaashatadu waa hay'ado iskood isku abaabulay kuwaas oo u furan cid kasta oo rabta in ay isticmaasho adeegyadooda islamarkaana aqbasha waajibaadka xubinnimada iyada oo aan lagu takooraynin jinsi, maqaamka bulsheed, qowmiyad, afkaar siyaasadeed, laxaadka jidheed iyo caqiido midnaba.

2/ Ururrada iskaashatadu waa in ay noqdaan hay'ado dimoqraadi ah kuwaas oo ay maamulaan xubnahooda doorka firfircoon ka qaataan dejinta siyaasadahooda iyo qaadashada go'aannadooda iyada oo dhamaan xubnuhu si siman u leeyihiin xaqa codaynta, halkii xubina uu leeyahay hal cod.

3/ Xubnuhu waxa ay helayaan macaash-wadaagga ka soo xarooda waxasoosaarka dheeraadka ah si ku salaysan saamigooda ay ku leeyihiin ururka iyo doorkooda ka qaybqaadashada kadib marka laga jaro ee kaydka lagu daro lacagaha ururku dhitaysto iyo adeegyada kale.

4/ Iskaashatadu waxa ay u madax banana tahay in ay heshiisyo la gasho dawlada iyo hay'adaha kaleba, in ay hanti ka hesho ilo kale oo ka baxsan raasamaalkeeda, balse waa in ay u martaa hab-dhaqan dimuqraadiyadeed oo aan dhaawacayn dhaqannada suuban ee gudaheeda

ሀ) ታማኝነት፤

ለ) ግልፀኝነት፤

ሠ) ማህበራዊ ኃላፊነት፤ እና

ረ) ለሌሎች ማሰብ፡

## ክፍል ሁለት

## ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረትና ምዝገባ

### ፯. ስለኅብረት ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አመሠራረት

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደ የባህሪያቸው ከመሠረታዊ እስከ ፌዴሬሽን በየደረጃው ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡

፪/ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር፡-

ሀ) በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነሙያ በተሰማሩ ግለሰቦች፤ እና

ለ) ቁጥራቸው ከሃምሣ በማያንሱ አባላት፤ ይደራጃል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ቢኖርም የሥራ ባህሪያቸውን እና የኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን መሠረት በማድረግ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመነሻ ቁጥርን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፤ ሆኖም የመነሻ ቁጥሩ ከ ፲ ሊያንስ አይችልም፡፡

፬/ በፌደራል ደረጃ የሚደራጅ መሠረታዊ ኅብረትሥራ ማህበር አባላት ነዋሪነታቸው ከሁለት እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ክልሎች የተውጣጡ ግለሰቦች መሆን አለባቸው፡፡

፭/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ በማደራጀት የሚመዘ ግብ ይሆናል፡፡

5/ Urur Iskaashatadu waa in ay waxbarasho iyo tababar siiso xubneheeda, wakiillada la doortay, gudoonka iyo shaqaalaha si ay kaalin uga geystaan horumrka bulshada; gaar ahaan dhalinyarada waxaa lagu baraarujiyo ururka iskaashatada macnihiisa iyo waxtarka uu leeyahay.

6/ Iskaashatadu waa in ay si haboon ugu adeegto xubnaha waana in ay xoojiso dhaqdhaqaaqa ururka iyada oo la shaqaynaysa kuwa heer Degaan, Dal, Qaaradeed iyo heer Caalami ba.

7/ Iskaashatadu waxa ay ka shaqayn doontaa horumarka waara ee bulshada deegaanka iyada oo isticmaalaysa Siyaasadaha ay ansixiyeen xubnaheedu.

### 6. Qiyamka (dhaqamada suubban) Ururrada Iskaashato iyo xubnahooda

1/ Dhaqamada suubban ee ururrada iskaashatada iyo xubnahooda waxa ay noqon doonaan:

a) is caawin
b) is xilqaan
c) kor u qaadista dhaqanka dimoqraadiyada
d) sinnaan
e) xaqsoor iyo
f) isku duubni

2/ akhlaaqiyaadka suubban ee xubnaha ururka iskaashatadu waxa ay noqon doonaan:

a) daacadnimo
b) kalfurnaan
c) islaxisaabtan
d) ka qayb qaadasho
e) masuuliyad bulsho iyo
f) is daryeel

## ፭. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቶች

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበር ምርት የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ወይም ምርት የማምረት እና አገልግሎት የመስጠት ሁለገብ ተግባር አጣምሮ የሚያከናውን ሆኖ ሊመሠረት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኅብረት ስራ ማህበራት በህግ በተከለከሉ የህዝብን ሞራላዊ እሴቶች በሚነኩ፣ የአካባቢን ደህንነት በሚጎዱ ተግባራት መደራጀት የማይቻል ሲሆን አግባብ ባለው ባለስልጣን የኢኮኖሚ አዋጭነት እንዲሁም በሚደራጁበት አካባቢ ሀብት መኖሩን በጥናት በመለየት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸውን የአማራጭ ዓይነቶች በማቅረብ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## ፮. የኅብረት ሥራ ስም

፩ / ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር መጠሪያ ስም ይኖረዋል፣ የስም አወጣጡም ምክንያታዊ፣ ሕግንና የሕዝብን ሞራል የማይቃረን መሆን አለበት፡፡

፪/ ከማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም መጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር የሚል" ሐረግ መጻፍ ይኖርበታል፡፡

፫/ አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት ስም፣ መለያ ምልክት እና የሥራ ክልል ውስጥ ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበር ተመሳሳይ እና አሳሳች ስም ወይም መለያ ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡

## QAYBTA LABAAD

## AASAASKA IYO DIWAANGELINTA URURKA ISKAASHATADA

### 7. Aasaaska Ururka Iskaashatada

1/ Ururrada iskaashato waxa loo aasaasi iyada oo lagu salaynayo heerka qaab-dhismeedkooda iyo shaqadooda laga bilaabo urur iskaashato oo aasaasi ah illaa heerka midowga.

2/ urur iskaashato aasaasi ah waxaa aasaasi kara

a) shaqsiyaad ka hawlgala aag isku mid ah, ama ku lug leh hawlo isku mid ah ama leh xirfad-aqooneed iyo takhasus isku mid ah.
b) tirada xubno aan ka yarayn konton qof.

3/ iyada oo aan la baalmaraynin tuduca (b) faqrada 2aad ee Qodobkan, cidda sharci ahaan ku shuqul leh ayaa awood u leh in ay habraaca jihaynta ururka ku xadiddo tirada ugu yar ee xubnaha ururka aasaasi kara iyada lagu salaynayo nooca shaqada iyo sahanka shaqo ee markaa la sameeyo. Iyada oo ay sidaas tahay, ururku kama yaraan karo 10 qof.

4/ ururka iskaashatada aasaasiga ah ee laga aasaaso heer federal waa in uu ka koobanyahay xubno kasoo kala jeeda labo dawlad-deegaan ama in ka badan.

5/ hay'adda ee ku shaqqda leh ayaa samayn doonta aasaaska iyo diwaangelinta ururrada iskaasho ee heer deegaan iyo heer federaal.

፬/ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ስም ጉልህ ሆኖ ተጽፎ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ በሚካሄድበት በማንኛውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት፡፡ እንዲሁም ፭/ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ፡፡

፭/ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ "የ ኅብረት ሥራ ማህበር" የ ሚለውን ስያሜ መጠቀም አይችልም፡፡

## ፲. ስለኅብረት ሥራ ማኅበር ምዝገባ

፩ / ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሆኖ ለመመዝገብ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል: -

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂዎች፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች በዚህ አዋጅና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠረት አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር መግለጫዎች፤

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን አድራሻ እና የተወካዮች ፊርማ፤

## 8. Noocyada Ururrada Iskaashatada.

1/ urur iskaashato waxa uu u dhisanyahay fulinta hawl waxsoosaar ama fulinta hawl adeegbixineed, hadii kale waxa uu u dhisanyahay fulinta labada hawloodba.

2/ iyada oo aan lagu xadgudbayn faqrada (1) ee qodobkan, noocyada ururrada iskaashatadu waa in aanay noqonin kuwo liddi ku ah qaanuunka, anshaxa suubban ee bulshada, fulinta hawlo waxyeellayn kara ammaanka deegaanka, kolkaa kadib waa in hay'adda sharci ee ku shaqqada leh in ay siiso ururka taageero xirfadeed/aqooneed kadib marka la sameeyo daraasad dhaqan-dhaqaale si loo ogaado awoodda dhaqaale ee lagu dhisi karo ururrada iskaashatooyinka.

## 9. Magaca Ururka Iskaashatada

1/ Urur kasta oo iskaashato waa in uu yeesho magac isaga u gaar ah, magacaasina waa in uu yahay mid maangal ah oo aan khilaafsanayn qaanuunka dawliga ah iyo dhaqanka hufan ee bulshada.

2/ Weedha "**ururka iskaashatada deymaha xaddidan ee**" waa in ay ka muuqato halka ugu horraysa ee magaca urur kasta oo iskaashato [marka ay af Somali tahay].

3/ Ururku ma isticmaali karo magaca iyo astaanta u diwaangashan urur kale, ama magac marin habaabin muujinaya, marka loo eego aagga ay ka hawlgasho iyo nooca shaqada.

4/ Magaca urur kasta oo iskaashato waa in laguo qoro khad jaamud ah laguna dhejiyo dhamaan goobaha uu ka hawlgalo ururku.

ሰ) ከሶስት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የስራ እቅድ ሰነድ፤

ሸ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ወይም ባንክ በሌለበት አካባቢ ከሆነ መዝጋቢው በወሰነው የፋይናንስ ተቋም መቀመጡን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሠራበት ቦታ መግለጫ

በ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የ ሚወሰኑ ሌሎች መግለጫዎች።

፫/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል። በዚህም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በኅብረት ሥራ ማህበርነት የተመዘገበበት ቀን ይጠቀሳል።

፬/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን የኅብረት ሥራ ማህበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደ ሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ወኪሎች ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መግለፅ አለበት።

፭/ የአመልካች ወኪሎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በጽሑፍ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ከሆነ፣ በክልል ሲሆን አግባብ ላለው የክልሉ ፍርድ ቤት ወይም በፌደራል ደረጃ ሲሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ፳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

Sidoo kale waa in lagu dul qoro ama lagu shaabbadeeyo dhamaan waraaqaha ka soo baxa ururka sida ogeysiisyada, farriimaha, bayaanada kale iyo dhamaan warqadaha lagu soo saaro magaca ururka iskaashatada.

5/ Ma jiro qof isticmaali kara magaca ururka isaga oo aan fasax ka haysanin hay’adda sharci ee ku shaqqada leh.

**10. Diwaaangelinta Ururka Iskaashatada**

1/ urur kasta oo iskaashato waa in uu iska diwaangeliyo hay’adda sharci ee ku shaqqada leh diwaangelinta ururrada iskaashatada

2/ urur kasta oo raba in loo diwaangeliyo urur iskaashato ahaan, waa in uu waraaqihiisa sharciga ah ku soo xaraysto hay’adda sharci ee ku shaqqada leh diwaangelinta gaar ahaan waa in uu haysto kuwan soo socda:

a) Hadal-reebta shirka xubnaha aasaasayaasha
b) xeer-hoosaadka ururka iyo sadex nuqul oo ka mida.
c) Magacyada, cinwaanka laga helo, iyo saxeexyada xubnaha gudiga maamulka ururka.
d) Magacyada, cinwaanka laga helo, iyo saxeexyada xubnaha gudiga dabagalka ururka.
e) Qoraal caddaynaya in dhamaan xubnaha ururkani ay buuxiyeen shuruudaha xubinnimada si waafaqsan bayaankan iyo xeer-hoosaadka ururka.
f) Hadii ururka iskaashatada la aasaasayaa yahay heer ka sarreeya heerka ururka iskaashatada aasaasi-

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገ በለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በሕጋዊ መንገድ የተመዘገ በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ለተፈቀደለት የሥራ መስክ ሌላተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው ይሠራል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረግጥ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገ ለግል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት ሰጥቶ የተቀሩት መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሟሉ ማስደረግ ይችላል፡፡

፱/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተቋቋ መበት ዓላማና መርህ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ ሕግ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊያግደው ይችላል፡፡

፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፱) መሠረት የታገደው የኅብረት ሥራ ማህበር ዕግዱ እንዲነሳለት በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካላመለከተ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ የ ማፍረስ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፲፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት የታገደ የኅብረት ስራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጥያቄውን የተቀበለውአግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና አግባብ ሆኖ ሲያገኘው እግዱንሊያነሳ ይችላል፡፡

ga ah, waxa looga baahan yhay magaca iyo cinwaanka xubinka ka socda ururka iskaashatada aasaasiga ah iyo saxeexa wakiilladooda.

g) Qorshe hawleedka ururka ee sadex illaa shan sanadood ah.

h) Waraaqo muujinaya caddadka raasamaalka lagu bilaabayo ururka iyo caddadka raasamaalka la isku darsaday ee lagu shubay akoonka bangi ee ururka. Hadii meesha aanu ka jirin wax bangi ah, waxa la dhigan karaa hay'adaha maaliyadeed ee ay hay'adda sharci ee ku shaqqada leh u xilsaartay.

i) Faahfaahin iyo macluumaad ku saabsan goobta iyo aagga-shaqo uu ka hawlgali doono ururku.

j) Iyo waxyaababaha kale ee ay u baahanyihiin sharciyada iyo awaamiirta qaabdhismeedka ururrada iskaashatadu ee hirgelinta bayaankan.

3/ Hay'adda sharci ee ku shaqqada leh diwaangelinta ururku waa in ay diwaangeliso ururka kadibna siisaa shahaadada dilwaangelinta ururka muddo shanta maalmood ee la shaqeeyo gudahood ah kadib marka ay ku qanacdo waraaqaha ururka iyo buuxintooda shuruudaha diiwaangelinta. Taariikhda aqoonsiga ururnimada waa in lagu caddeeyo shahaadada diiwaangelinta ururka maalinta la diiwaangeliyey.

4/ Hadii hay'adda sharci ee ku shaqqada leh diiwaangelinta ururradu ay diiddo in ay diiwaangeliso ururka, waa in ay xubnaha wakiillada ururka siiso warqad qoraal ah oo sharraxaysa sababta loogu diiday diwaangelinta muddo ka bilaa-

አግባብ ያለው ባለሥልጣን እግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቃል። አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አካል ዕግዱ የተሰጠው በፌደራል ደረጃ ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ዕግዱ በክልል ደረጃ ከሆነ ስልጣን ላለው ለክልሉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

## ፲፩. የሕግ ሰውነትና ኃላፊነት

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሠረት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ይኖረዋል።

፪/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፤ ኃላፊነቱ ተወሰነ ነው።

## ፲፪. የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳዳሪያ ደንብ

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፣ የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል:-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አድራሻ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማና ተግባር፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ ቦታ እና አካባቢ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎችን፤

ሠ) ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች፤

banta maalinta laga qabtay waraaqaha illaa maalinta shanaad ee ka mida maalmaha shaqada.

5/ Hadii xubnaha wakiillada ururku ay cabasho ka soo celiyaan warqada faahfaahinta sababta diidmada ee ay siisay hay'adda diiwaangelinta ururradu sida uu dhigayo faqrada (4) ee Qodobkan, waxa ay arji dacwadeed u gudbisan karaan maxkamada ay qusayso ee heer deegaan hadii ay iskaashatadu tahay heer deegaan, hadii ay tahay heer federaalna maxkamada sare ee ay qusayso ee heer federaal, muddo 60 cisho oo xidhiidh ah gudahood maxkamada xukunkan qaadi karta.

6/ Shahaadada diiwaangelinta ee la siiyay ururka iyada oo la raacayo faqrada (3) ee Qodobkan, waxa ay si buuxda u caddaynaysaa in ururka iskaashatadu yahay mid diwaangashan oo haysta sharciyadda bayaankan 985/2016.

7/ Urur kasta oo iskaashato oo si sharci ah ugu diiwaangashan faqrada (3) ee Qodobkan, waxa uu gudo geli karaa shaqooyinkiisa si waafaqsan ujeedooyinkiisa iyo hawlahiisa ku cad xeer-hoosaadkiisa laga bilaabo taariikhda xiliga la diwaangeliyey iyada oo aan habayaraatee lagu xidhaynin wax ruqsad ah oo intaas ka baxsan.

8/ Hadii hay'ada sharci ee ku shaqqada leh diwaangelintu ay xaqiijiso in ururku buuxiyey shuruudaha ku xusan tuducyada (a) illaa (h) ee faqrada Qodobkan, waxa ururka la siinayaa shahaado ku meelgaadh ah oo shaqaynaysa muddo aan ka badnayn hal sano si markaa kadib loo hubiyo in ururku muddadaas ku soo

ረ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር አካላት

ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር፤

ሰ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስለሚወጡበትና ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ሸ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ፣ ሹመትና የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ቀ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ስብሰባ አጠራር እና ስለድምጽ አሰጣጥ፤

በ) ስለትርፍ አመዳደብና ክፍፍል፤

ተ) ስለሂሣብ ምርመራ፤

ቸ) ስለሠራተኛ አቀጣጠር፤ ኀ) ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጣ ደንብ እና መመሪያን የማይቃረኑ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ልዩ ውሣኔ ሊሻሻል ይችላል፤ ሆኖም የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳዳሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊጸና የሚችለው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

፫/ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የመተዳደሪያ ደንብእንዲሻሻል በጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን የተደረገ ው ማሻሻያ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የተላላፈ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ በሦስት ቅጅ ተደርጎ ዉሳኔ በተላለፈ በ፲ ፭ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡ ማሻሻያ በተጠቀሰው ቀን ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

dhammaystiray shuruudaha intii ka dhinayd.

9/ Hadii ururka iskaashatada lagu helo in uu ka shaqaynayo wax ka baxsan ujeedooyinkiisa iyo mabaadii'da u degsan, hay'ada ku shaqqada leh waxa ay awood u leedahay in ay xayiraad ku soo rogto ururka islamarkaana ka joojiso dhamaan shaqooyinkiisii sharciga ahaa.

10/ Maadaama xayiraad lagu soo rogay ururka iskaashatada iyada oo la cuskanayo faqrada (9) ee Qodobkan, hadii fashil ku yimaaddo in xayiraadda laga qaado muddo 30 maalmood oo xidhiidh ah gudahood, hay'adda sharci ee u qaabilsani waxa ay awood u yeelanaysaa in ay sifo sharci ah ku xaraashto (lacagayso) hantida ururka.

11/ Hadii shirweynaha guud ee ururka la xayiray iyada oo la raacayo faqrada (9) ee Qodobkan ay soo gudbistaan codsigooda ku aaddan in laga qaado xayiraadda kadibna hay'adda sharci ee qaabilsani ay xaqiijiso in codsigu yahay mid sax ah, waa in xayiraadda ururka laga qaado. Balse hadii hay'adda sharci ee qaabilsani ay ka qaadiweydo xayiraadda, waa in ay ururka siiso warqad qoraal ah oo sharraxaysa sababta looga qaadi waayay xayiraadda. Dhinac kasta oo aan ku qancin go'aamada ka soo baxay heer federaal waxa uu arji dacwadeed u gudbisan karaa maxkamada sare ee federaalka, hadii arrintu ay tahay heer deegaanna waxa uu u gudbisan karaa maxkamada sare ee deegaanka u qaabilsan xukun ka gaadhista arrintan.

**11. <u>Gudiyada Garsoorka iyo xilalkooda</u>**

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የቀረበው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ እና መመሪያ የማይቃረን መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥ ማሻሻያውን ይመዘግባል፤የምዝገባ ማስረጃውንም በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል።

፭/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻያ ካልመዘገበ ወይም ማይመዘግብበትን ምክንያት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ካላሳወቀ የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ እንደተመዘገበ ተቆጥሮ በሥራ ላይ ይውላል።

፮/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መርሆዎች እና እሴቶች ማካተት አለበት።

፯/ ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር በማህበሩ የአመራር አካላት አባልነት ውስጥ የሴቶችን ተሣትፎ ለማሣደግና ለማበረታታት የሚያስችል መስፈርት ማካተት አለበት።

፰/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሴቶችን፣የወጣቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ የሚያሳድጉ ተግባራትን በስትራቴጂክ እና በዓመታዊ እቅዶቹ ውስጥ ማካተት አለበት።

**፲ ፫. ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ውህደትና መከፋፈል**

፩ / የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ በልዩ ውሣኔ፡- ሀ) ራሱን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊከፋፍል፤ ወይም ለ) ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ

1/ Urur kasta oo iskaashato oo si sharci ah ugu diwaangashan qodobka 10aad ee Bayaankan waa in uu yeesho gudi garsoor laga bilaabo maalinta diwaangelinta.

2/ Urur kasta oo iskaashato ma qaadi karo masuuliyadda hanti ka badan wadarta raasamaalkiisa guud ee saafiga ah, waana in masuuliyadiisu xaddidnaato.

**12. Xeer-Hoosaadka Ururka Iskaashatada**

1/ Urur kasta oo iskaashato waa in uu yeesho xeer-hoosaad u gaar ah, kaas oo gudihiisa ay ku cadyihiin qodobadan soo socda:

a) Magaca iyo ciwaanka ururka
b) Ujeedooyinka loo aasaasay iyo hawlaha uu qabto ururku
c) Goobta uu ka hawlgalo iyo xarunta uu ka shaqeeyo ururku
d) Shuruudaha qaadashada xubinnimada ururka
e) Xilalka iyo xuquuqaha xubnaha ururka
f) Awoodaha, masuuliyadaha iyo waajibaadada gudiga maamulka ururka iskaashatada
g) Shuruudaha ka bixitaanka iyo ka xayuubinta xubinnimada ururka
h) Shuruudaha doorashada, magacaabista, muddada xil haynta, xayiraadda iyo eriga xubnaha guddiga maamulka iyo laamaha kale ee wax ka maamula ururka.
i) Shuruudaha ku baaqista shirarka iyo hab codbixinta ururka
j) qoondaynta iyo wadaagga faa’dada
k) hantidhawrista
l) hanaanka shaqaalaysiinta ururka

ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመዋሃድ አዲስ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሊመሠርት፤ይችላል፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማኅበር መዋሃድ ወይም መከፋፈል ልዩ ውሣኔ ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት እና ዕዳ ጠያቂዎች በመዋሃዱ ወይም በመከፋፈሉ የተስማሙበት መሆኑ፤ ወይም

ለ) ያልተስማሙ አባላትና ዕዳ ጠያቂዎች የተከፈላቸው መሆኑ ወይም የክፍያ ዋስትና የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጦ ልዩ ውሣኔው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገ በመሆኑ፤

ሐ) የቀድሞው የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ኅብረት ሥራ ማህበር ምዝገባ ከመዝገብ መሰረዙ እና በውህደት ወይም በመከፈሉ የተፈጠረ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር መመዝገቡ፤ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

፫/ በውህደቱ ህልውናቸውን ያጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መብት እና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማህበር ልዩ ውሳኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበር ይተላለፋሉ፡፡

፬/ በመከፋፈሉ ሕልውናውን ያጣው የኅብረት ሥራ ማህበር መብት እና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ልዩ ውሣኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋሙት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ይተላለፋሉ፡፡

m) iyo qodobo kale oo aan ka hor imanaynin bayaankan, shUruucda iyo awaamiirta hirgelinta bayaankan.

2/ Wax ka bedelka xeer-hoosaadka ururka waxa lagu samayn karaa qaraar aan caadi ahayn oo ka soo baxa shirweynaha golaha, haseyeeshee wax ka bedelka xeer-hoosaadka ururku waxa uu dhaqan-gal noqonayaa ka dib taariikhda la soo gudbiyo ee ay diwaangeliso hay'adda sharci ee u qaabilsan.

3/ Hadii ururka iskaashatadu uu go'aansado in uu wax ka bedelka ku sameeyo xeer-hoosaadkiisa sadex nuqul oo wax ka bedelkii ah iyo qaraalkii lagu soo saaray shirweynaha golaha guud oo la waafajiyey bayaankan waa in loo soo gudbiyo hay'adda sharci ee ay qusayso muddo 15 cisho oo maalmaha shaqada ah gudahood laga bilaabo maalinta go'aanka wax ka bedelka la soo saaray. Hadii wax ka bedelka lagu sameeyey xeer-hoosaadka loo gudbin waayo hay'adda sharci ee ay qusayso muddada la cayimay gudeheeda lama aqbali doono.

4/ Hay'adda sharci ee u qaabilsani waa in ay aqbasho diwaangelinta waxka-bedelka xeerka ee ku cad faqrada (3) ee Qodobkan, kadib marka ay xaqiijiso in uu waafaqsanyahay bayaankan iyo shuruucda iyo awaamiirta hirgelinta bayaankan waana in ay bixiso caddayn ku saabsan diwaangelinta wax-kabedelka xeerka muddo shan cisho oo xidhiidh ah oo maalmaha shaqada ah gudahood.

## ፲፬. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ይደራጃሉ፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬንን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ እየ ታየ ማደራጀት የሚቻል ይሆናል፡፡

፫/ በፌደራል ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባላት ቢያንስ ከሁለት ክልሎች የተውጣጡ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መሆን አለባቸው፡፡

## ፲፭. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አደረጃጀት

፩/ ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ይደራጃል::

፪/ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ ታይቶ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽንን በፌደራልወይም በክልል ደረጃ ማደራጀት ይቻላል፡፡

፫/ በፌደራል ደረጃ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አባላት ቢያንስ ከሁለት ክልሎች የተውጣጡ ሁለት እና ከዚያ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች መሆን አለባቸው፡፡

## ፲፮. በሙያ የሚደራጅ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ማሟላት ያለበት መስፈርቶች

፩/ ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራማህበር የአባላትን ሙያ መሠረት አድርጎ የሚደራጅ ከሆነ እያንዳንዱ አባል ከሚመለከተው አካል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::

5/ Hadii hay'adda sharci ee u qaabilsani ay ku fashilanto diwaangelinta waxka-bedelka xeer-hoosaadka ururka ama bixinta caddayn ku saabsan in ay diiwaangelisay waxka-bedelka marka loo gudbiyo kadib, waxka-bedelka xeer-hoosaadka waxa loo tixgelinayaa mid diwaangashan sidaas ayuuna dhaqangal ku yahay.

6/ Urur kasta oo iskaashato waa in uu xeer-hoosaadkiisa ku caddeeyo qiyamka iyo mabaadii'da uu ku shaqaynayo.

7/ Urur kasta oo iskaashato waa in uu yeesho qodobo dhiirrigelinaya doorka haweenka ee ka qayb noqoshada gudiga maamulka ururka

8/ Urur kasta oo iskaashato waa in uu istiraatijiyadiisa iyo qorshe sanadeedkiisa ku daro hawlo loogu talo galay in lagu dhiirri geliyo haweenka, dhalinyarta iyo dadka naafada ah.

## 13. Midowga iyo kala tagga ururrada iskaashatada

1/ Ururka iskaashatadu waxa uu shirweynaha golaha guud ku soo saari karaa qaraar aan caadi ahayn kaas oo:

a) Ururku isugu qaybinayo labo urur ama in kabadan
b) In ay ku midoobayaan labo urur ama in ka badan si ay u noqdaan hal urur iskaashato

2/ Qaraarka aan caadiga ahayn ee midowga iyo kala tagga ururradu waxa uu dhaqangal noqonayaa kadib marka la caddeeyo:

a) In xubnaha iyo lacag deymiyeyaasha ururka isku raaceen midowga ama kala tagga labada urur

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚቀርብባቸው በህግ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያወጡ በሚያስገድዱ የስራ መስኮች ብቻ ላይ ይሆናል።

፫/ የሙያ የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴት ጨምረው ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡

**<u>፲፯. ስለ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ አደረጃጀት</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒ ዬኖችን እና ፌዴሬሽኖችን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚወክል ሊግበአገር አቀፍ ደረጃ ሊመሠርቱ ይችላሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመሰረት ሊግ ቁጥር ከአንድ ሊበልጥ አይችልም።

፫/ የሊግ አደረጃጀት፣ ተግባራትን እና የፋይናንስ ምንጭ በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤትበሚወጣ ደንብ ይሰወናል።

**<u>፲፰. የኅብረትሥራማህበራት ግዴታ የኅብረት ሥራ</u>**

ማህበራት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡-

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባሎቻቸው የሚፈልጉትን አገልግሎት በተያዘው ዕቅድ መሠረት የማቅረብ፤

፪/ በአገሪቱ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለቀጠሯቸው ሠራተኞች መብታቸውን የመጠበቅ፤

፫/ የኅብረት ስራ ማህበራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ከገቢ ግብር በስተቀር ሌሎች ለመንግስት መክፈል

In xubnaha iyo lacag deymiyeyaasha ururka diiday qaraarka midowga iyo kalatagga la siiyey xaqii iyo saamigii ay ku lahaayeen ururka ama kadib marka la caddeeyo in qaraarka lagu xusay damaanad qaadka saamiga iyo xuquuqahooda taas oo loo gudbiyey ayna aqbashay laanta dawliga ah ee ay qusayso.

b) Diiwaangelinta/sharciyadda labada urur ee hore ama ururka hore ee laga saaray diiwaanka sharciga ah kadibna midowga ururka ama labada urur ee cusub ee kala baxay si cusub loo diwaangeliyo loona sharciyeeyo.

3/ xuquuqaha iyo waajibaaddada ay lahaan jireen labada urur ka hor intii aanay isku biirin waxa loo wareejin doonaa ururka cusub ee ka dhashay midowga labada urur sida ku cad qaraarkii aan caadiga ahayn ee ay ku midoobeen kaas oo waafaqsan faqrada (2) ee qodobkan.

**14. <u>Aasaaska Dallada Ururrada Iskaashatooyinka</u>**

1/ Dallada Ururrada Iskaashatooyin-ka waxa samayn kara labo ama in ka badan oo ka mida ururada iskaashatooyinka aasaasiga ah kuwaas oo wadaaga ujeedooyin isku mid ah.

2/ Ururka Dallada Iskaashatooyinka waxa laga dhisi karaa heer federaal ama heer deegaan iyada oo lagu salaynayo suurtagalnimada iyo xaaladdooda dhaqan dhaqaale.

3/ Xubnaha Dallada Ururrada Iskaashatooyinka ee laga aasaasayo heer federaal waxa laga soo qaadan doonaa ugu yaraan labo urur iskaashato aasaasi ah oo ka soo kala jeedaa labo dawlad deegaan oo kala duwan.

የሚገባቸውን ክፍያ በሕጉ መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የማድረግ፤

፬/ የመተዳደሪያ ደንቡን አክብሮ የመስራት፤

፭/ ለሚመለከተው አካል አስፈላጊውን መረጃ በተጠየቁ ጊዜ የመስጠት፤

፮/ የተቋቋሙበትን መርህ እና ዓላማ አክብረው የመስራት፡፡

## **<u>፲፱. ሥራ ስለመጀመር</u>**

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ በዕቅዱ መሠረት ሥራ ካልጀመረ በተጨማሪ በሦስት ወር ውስጥ እንዲጀምር ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጠውየማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ሥራ ካልጀመረ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሣብ ከተጣራ እና መፍረሱ ከተወሰነ በኋላ ምዝገባው ተሰርዞ ሕጋዊ ሰውነቱን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

## **<u>፳. የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማሳደስ</u>**

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሞ ከተመዘገበበት እና ሕጋዊ ሰውነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በወጣው መመሪያ መሠረት በየሦስት ዓመቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## **15. <u>Aasaaska Midowga Ururrada Iskashatooyinka</u>**

